# ከእግዚአብሔር ፍቅር

... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ ፡ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ። ኢሳ 48 ÷ 17

God's Love, P.O.Box 6734, Lee's Summit MO 64064. E-mail – glnlm@ethiogodslove.org አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ

www.ethiogodslove.org 1ኛ ደብዳቤ 2007 እአአ 1st Quarter 2007

ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13


“እግዚአብሔር ሆይ! አንተን ማመስገን÷ልዑል ሆይ! ስለ ክብርህ መዘመር እንዴት መልካም ነው! ስለ ዘላለማዊ ፍቅርህ በየማለዳው መናገር ÷ ስለ እውነተኝነትህ በየሌሊቱ ማውራት÷እንዴት መልካም ነው! ባለ አውታር በሆኑ የሙዚቃ መሣርያዎችና በበገና ቅኝት÷ አንተን ማመስገን እንዴት መልካም ነው! እግዚአብሔር ሆይ ! የአንተ ታላላቅ ሥራዎች ደስ ያሰኙኛል፤ አንተ ስላደረግሃቸውም ነገሮች በደስታ አዘምራለሁ። እግዚአብሔር ሆይ! ሥራህ እንዴት ታላቅ ነው ! አሳብህስ እንዴት ጥልቅ ነው! ሰነፍ ሰው ሊያውቀው÷ ሞኝም ሊያስተውለው አይችልም። (መዝሙረ ዳዊት 92÷1-6 አ/ት)

# መወደድ

“ዳዊትም ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች÷ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው” (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 18÷1)

“ዮናታንም ዳዊትን፦ ነፍስህ የወደደችውን ሁሉ አደርግልሃለሁ አለው፦” (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 20÷4)

ጊዜው የኢኮኖሚ ቀውስ (ሪሴሽን) ወይም ሐገራዊ የኢኮኖሚ ማሽቆልቆል በአሜሪካ የተከሰተበት ወቅት ነበረ፡ እንዲህ ባለ ጊዜ ታላላቅ ትርፎችን በማስገኘት የከበሩና የተመሰገኑ ኩባኒያዎች ዕዳ በዕዳ በመሆን ይከስራሉ።

የቆየ ወዳጅነት ፍቅርና መግባባት የነበራቸው አቶ ማርሊና አቶ ሮበርት የሚባሉ ጓደኛሞች ነበሩ። እነርሱም በንግዱ ዓለም እጅግ የሚስማማሙና እንደ መንታ ልጆች የሚጣጣሙ ጥሩ ወዳጆች ነበሩ። ስለዚህ አንዱ የንግድ ውሳኔ ማድረግ ከብዶት ወይም በሌላ ጉዳይ ተወጥሮ የጨነቀው ዕለት ወደ ሌላኛው ሄዶ የልቡን ሸክም በማካፈል ይጽናና ነበር።

አቶ ማርሊም በዚያ የኢኮኖሚ ቀውጢ ወቅት እጅግ ብዙ ገንዘብ ከከሰሩት ነጋዴዎች አንዱ ነበር። እርሱም ከደረሰበት ጭንቀት የተነሣ ወደ ወዳጁ አቶ ሮበርት ሄደና አጫወተው። አቶ ማርሊ ብሶቱን ተናግሮ ለመጨረስ ሁለት ሰዓት ያህል ፈጀበት። የአቶ ማርሊ ወዳጅ አቶ ሮበርትም የወዳጁን ንግግር በትዕግስት ሳያቋርጥና ምክር ለመስጠት ሳይቸኩል ያዳምጥ ነበር። አቶ ማርሊም ንግግሩን ከፈፀመ በኋላ ከጓደኛው የሚመጣውን መልስና ምክር ለመስማት በጉጉት ይጠባበቅ ጀመር።

ዳሩ ግን የአቶ ሮበርት መልስና ምክር አጭር ነበረ። እርሱም “ለዚህ ችግርህ የሚሆን መፍትሄ አላውቅም። ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ። ያለኝን ተካፍለን ይህን ክፉ ጊዜ አብረን እናሳልፋለን እንጂ÷ እኔ በልቼ እያደርሁ÷ አንተና ቤተሰብህ ጾማችሁን አታድሩም።” የሚል ነበር።

አቶ ማርሊ ይህን በሰማ ጊዜ በቃላት በማይገለጽ መጽናናት ተሞላ። የወዳጁ ከጎኑ መቆም የተስፋን መብራት በልቡ ለኮሰለት። ወድያውም አስገራሚ የንግድ ራዕዮችን ማስተዋል ጀመረ። የሚያስደንቁ ብሩህ ውሳኔዎችንም በማድረግ ኩባኒያውን ከኪሳራ አውጥቶ ያን ክፉ ወቅት ለማለፍ ቻለ።

አይገርምም? አቶ ማርሊ ችግሩን የተወጣው ከወዳጁ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ርዳታ በመቀበል አይደለም። ተስፋ በማግኘት ነው። ተስፋም ጭንቀት ያጨለመውን አእምሮውን አበራለት። ችግሩንም ያሸነፈው በብሩህ አእምሮው አስተዋይ ውሳኔዎችን በማድረግ ነው።

“እንዲህም ከሆነ÷እምነት፡ተስፋ፡ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።”
1 ቆሮንቶስ 13÷1

## የቅርብ ወዳጅ (የልብ ጓደኛ)አለህ?

አልፎ አልፎ ምሣ የምትገባበዙትን ማለቴ አይደለም። አንዳንዴ ስልክ የምትደዋወሉትንም አይደለም። ባመቸ ጊዜ ተገናኝታችሁ የምትጸልዩትንም ሳይሆን በዕውነት የሚቀርብህ የልብ ወዳጅ አለህ?

ተማሪ በነበርክበት ጊዜ የነበረህ ዓይነት÷ከእርሱ የምትደብቀው የሌለህ÷ እርሱም የሚደብቅህ የሌለው?ብትስቅ ቀላል÷ ብታለቅስ ደካማ የማይልህ፦ ሲሳካልህ ጎሽ÷ሲበላሽብህ አይዞህ የሚልህ? ስታጠፋ የሚገስጽህ ÷ ሲከፋህ የሚያጽናናህ? ቢቸግረው የማትጨክንበት÷ ቢጎድልብህ ሳያቅማማ የሚሞላልህ ወዳጅ አለህ ? በአጭሩ በመከራ የጨነቀህ ቀን መጠጊያ የሚሆንህና አንተም የምትሆነው ወዳጅ አለህ?

ለመሆኑ እንደዚህ ያሉ ጓደኞች በዚህ ዘመን ወዴት ናቸው? በወጣትነት ዘመን እንደ ነበሩን ያሉ÷ታማኝ ጓደኝነቶች በጉልምስና ዘመን ማግኘት የሚያስቸግረው ለምንድን ነው? መልሱን ለሁላችን መተው ይሻላል።

ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ (የልብ) ወዳጅ ያስፈልገዋል። የኑሮ ስኪት ያስከረውም ሆነ፡ ሽንፈት ያደቀቀውም የቅርብ ጓደኛ ሊኖረው ይገባል። ያውም ለወንድ ክርስቲያን ወንድ÷ ለሴትም ሴት- ጓደኛ ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም እንዲህ ያለ ቅርብ ጓደኝነት በተቃራኒ ጾታ መሐከል (ከትዳር ውጭ) ጤነኛ ሆኖ ሲቀጥል ስለማይታይ ነው።

በአቅመ አዳም ዕድሜ አብዛኛው ሰው ያለውና ጓደኛ የሚላቸው÷ በሥራ ቦታ አብረውት የሚውሉትንና የሥራ ሁኔታ ያፈራውን መተዋወቅ ነው። ይሁን እንጂ የሥራ ቅርርብ አብዛኛውን ጊዜ የጠበቀ ወዳጅነት ሲፈጥር አይታይም።

አብዛኛው ሰው የዕውነተኛ ጓደኛ ኪሳራ ያጠቃው ነው። የቅርብ ወዳጅ ፈልጎ ማግኘትም ሆነ ማዳበርም አያውቅም። ራሱም ለሌሎች ጥሩ ወዳጅ መሆን እንዳለበት አያውቅም። ከብዙ ሕዝብ ጋር ይተዋወቃል። ነገር ግን የልብ ጓደኛ በማጣት በብቸኝነት የተጠቃ ሕይወት ይኖራል።

የቅርብ ጓደኛ የሌላቸው ወይም ከቅርብ ወዳጆቻቸው በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነጠሉ ሰዎች (ዲፕሬሽን) ለሚባለውና ለሌሎችም የአእምሮ ሕመሞች በቀላሉ የተጋለጡ መሆናቸውን የሕክምና ባለሙያዎች ይመሰክራሉ።ሰዎች ነፍሳቸውን በገዛ ራሳቸው የሚያጠፉት በእነዚህ ሁኔታዎችና በመሳሰሉት ምንያት ነው።

ጥሩ ጓደኛ ማግኘትም ሆነ የተገኘውን በጥንቃቄ ማጽናት ዋጋ ያስከፍላል። ከህደት÷መዋረድ÷ መቆሳሰል ሊከሰቱ ይችላሉ። ነገር ግን የጓደኝነትን ጥበብ ተግተን ብንማርና ብናስተውል ታማኝ ወዳጅ ማግኘት ብዙ ወርቅና ብር ከማግኘት የተሻለ ሆኖ እናገኘዋለን።

ምናልባት ከአንድ በላይ ጓደኛ ይኖረሃል። ወይም አንድም የቅርብ ወዳጅ የለህም። ምናልባት ከብዙ ሰው ጋር ጥሩ ትውውቅ አለህ። ሆኖም አንዳቸውም ለክፉ ቀን አይገኙልህም።ምናልባት የጓደኛን ጥቅም በአግባቡ ስላልተረዳህ በቂ ጥንቃቄና ርምጃ ወስደህ

አታውቅም:: የሚከተሉት መጠይቆች በዚህ አኳያ ሊረዱ የሚችሉ ናቸው:-

1. ሲከፋህና የልብህን የምታካፍለው ሲያሻህ የምትሄድበት ወዳጅ አለህ?

2. ይንቀኛል÷ ይገምተኛል ሳትል የልብህን የምትገልጥለት ሰው አለህ?

3. በከፋህ ቀን ለመምከር ሳይቸኩል ቁጭ ብሎ በትዕግስት በማዳመጥ የሚያናግርህ ወዳጅ አለህ?

4. በተሳሳትህ ጊዜ ወይም ባጠፋህ ጊዜ ወይም ኃጢአት ስታደርግ አይቶ÷ ይጠላኛል ሳይል የሚገስጽህ ወዳጅ አለህ?

5. በኃጢአት ብትወድቅና ሁሉ ቢከዳህ ብቻውንም ቢሆን ከአንተ ጋር የሚቆም÷የማይከዳ ወዳጅ አለህ?

6. እንደ አቶ ሮበርትና አቶ ማርሊ÷ቁሳዊ ድጋፍ ቢያስፈልግህ ያለውን የሚያካፍልህ ታማኝ የክፉ ቀን ወዳጅ አለህ?

7. ከሰው ሁሉ ጋር የማይካፈሉትን ሚስጢርህን ብትነግረው እንደ ራሱ ነገር አድርጎ የሚጠብቅልህ ጓደኛስ አለህ?

8. ከወዳጅህ ጋር ለጸሎት እና ለመጠያየቅ ምን ያህል አዘውትራችሁ ትገናኛላችሁ?

9. አንተ ራስህ ለወዳጆችህ ታማኝ ነህ?

## ወዳጅነት (ጓደኝነት) የማይጸናበት ምክንያት ምንድን ነው?

ከአንዱ ወይም ከሁለቱም ወገን ፍቅር ባለመኖሩ ወይም ባለመጠበቁ ነው:: መልካም ወዳጅነት ያለ ፍቅር ሊኖር ስለማይችል የፍቅርን ዕውነተኛ ትርጉም ተረድቶ መለማመድ ያስፈልጋል:: ዕውነተኛ ፍቅር እንደሚከተለው በመጽሐፍ ተገልጾ ይገኛል::

"ፍቅር ይታገሣል÷ ቸርነትንም ያደርጋል፤ፍቅር አይቀናም፤ፍቅር አይመካም፤ አይታበይም ፤ የማይገባውን አያደርግም÷የራሱንም አይፈልግም÷ አይበሳጭም በደልን አይቆጥርም ፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም፤ሁሉን ይታገሣል÷ሁሉን ያምናል÷ሁሉን ተስፋ ያደርጋል÷በሁሉ ይጸናል::"
(1ቆሮንቶስ 13÷4-7)

ከዚህ በላይ በተመለከተው ቃል መከበር ወይም አለመከበር ወዳጅ ማግኘት ወይም ማጣት እንደሚቻል ዕውቅ ነው:: መቼም ሰው የዘራውን ማጨዱ የተጻፈ ነውና ፍቅርን የሚፈልግ ያንኑ መዝራትና እግዚአብሔር እንዲያበዛለት መጸለይ አማራጭ የለውም:: የእግዚአብሔር ሰው ስለሚያስፈልገው ነገር እንደሚጸልይ ሁሉ:- ጓደኛንም እንዲሰጠው እግዚአብሔር አምላኩን በጸሎት መጠየቅ አለበት::

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ጥያቄዎች ወዳጅን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ለመሆንም የሚረዱ ጠቋሚዎች እንዲሆኑ ቀርበዋል:: ጓደኞች እያሳቸው÷ ባለማስተዋል÷በቸልታ የሚመለከቱ ሰዎችንም ስለሚያነቃቁ ከብዙ አኳያ ሊጠቅሙ እንደሚችሉ እገምታለሁ:: ጌታ ለዳዊት ዮናታንን እንደ ሰጠ ÷ ላንተም ታማኝ ወዳጅ ይስጥህ:: አንተንም ታማኝ ወዳጅ ያድርግህ:: አሜን::

(The man in the mirro) ከተባለ መጽሐፍ ተወስዶ ተዘጋጀ::



መልዓከ ገብሪኤል

መልዓከ ገብሪኤል ከቅዱሳን መላእክት አለቆች አንዱ ነው:: ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ለነብዩ ዳንኤል በተገለጸው ራዕይ (በትንቢተ ዳንኤል 8÷16 እና 9÷21) እንደምናነበው:- በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የመጥምቁ ዮሐንስንና የጌታ ኢየሱስን ልደት ለማብሰር በተገለጠ ጊዜ (በሉቃስ ወንጌል 1÷19 እና 26) ተመልክቷል ::

ቅዱሳን መላዕክትን በአጠቃላይ በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊና አፈታሪካዊ አመለካከቶች አሉ:: አፈታሪካዊው ብዙ ሲሆን÷ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ግን በዮሐንስ ራዕይ 22÷ 8-9) የሚገኘው ነው:: እርሱም እንዲህ ይላል:-

"ይህንንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ:: በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልዓኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ:: እርሱም:- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ÷ ከአንተ ጋር÷ ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር÷ የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ::" ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውነት ለመላዕክት መስገድ በእግዚአብሔር ቃል ያልተደገፈ መሆኑን ያሳምናል::

ይህ ብቻ ሳይሆን የማማለድንም ኃላፊነት አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያስተምረናል::

"አንድ እግዚአብሔር አለና÷በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ ÷ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ÷..." (1ጢሞቴዎስ 2÷5) ደግሞም:-

"የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው÷ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው÷ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው::"ይላል:: (ሮሜ 8÷34)

ስለዚህ አምላክና ፈጣሪ ሆኖ እያለ÷ ክብሩን ትቶ ወርዶ÷በሰው አምሳል በቅድስና ተወልዶ÷ነፍሱን ለሰው ልጆች ቤዛ አድርጎ ሰጥቶ÷ሞትንም ሲያልንም አሸንፎ በአብ ቀኝ የተቀመጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የማዳንም የማማለድም ሥልጣንና ችሎታ አለው::

# እግዚአብሔርን መስማት

ፀሎቴ ተመልሶ እንደ ሆነ እንዴት አውቃለሁ? ይህ በዘመናት ሁሉ የነበረ ጥያቄ ነው:: የዕምነት አባቶችም ጥያቄ ነበረ:: ፀሎታችንን በእግዚአብሔር ፊት ካቀረብን በኋላ መልሱ ሁል ጊዜ ግልጽ ሆኖ አይታይም:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ፀሎትን ሰምቶ የሚመልስ አምላክ ለመሆኑ አያከራክርም::

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ጌታ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር የሚነጋገርበት መንገድና አኳኋን ብዙ ነው ከዚህ ቀጥሎ እግዚአብሔር የተናገረባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶችና ሁኔታዎች ከቃሉ እንመለከታለን::

የእግዚአብሔር ካሕን የነበረው ዘካሪያስና ባለቤቱ ኤልሳቤጥ÷ልጅ አልነበራቸውም:: ኤልሳቤጥ መካን ነበረች:: ስለዚህም ነገር ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ይፀልዩ ነበር:: የሉቃስ ወንጌል 1÷8-13 እንዲህ ይላል:-

"እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል÷እንደ ካሕናት ሥርዓት ወደ ጌታ ቤተ-መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት:: በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር:: የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው:: ዘካሪያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ ÷ ፍርሐትም ወደቀበት:: መልአኩም እንዲህ አለው :- ዘካሪያስ ሆይ! ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ: ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች: ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ::"

በሌላ ሁኔታ ደግሞ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 18÷9-10 የተመለከተውን እናገኛለን:: ሐዋሪያው የጌ

ታ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በትጋት በመስበኩ ምክንያት ማስፈራራትና ማሳደድ ይደርስበት ነበር። በዚያን ጊዜ የጌታ መልስ የመጣው በራዕይ መልክ ነበር። እንዲህ ይላል፦
"እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ ነገር ግን ተናገር፥ዝምም አትበል፤በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው።"

እንዲሁም በሌላ ሁኔታ እግዚአብሔር ከዚህ በተለየ መንገድ ሲናገር እናገኛለን። የናቡከደነጾር ልጅ ብልጣሶር ከኢየሩሳሌም የተማረኩ ክቡርና ቅዱሳን ዕቃዎች በቤተመንሥቱ ውስጥ ነበሩት። ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ ድግስ ላይ በሰከረ ጊዜ የከበሩትን ዕቃዎች አስወጥቶ ተጠቀመባቸው። የእግዚአብሔርም ዕቃ ክብር ከመደፈሩ የተነሣ የቁጣው መልዕክት መጣ። "በዚያም ሰዓት የሰው እጅ ጣቶች ወጥተው በንጉሡ ቤት በተለሰነው ግምብ ላይ በመቅረዙ አንጻር ጻፉ፥ ንጉሡም የሚጽፉትን ጣቶች አየ።የዚያን ጊዜም የንጉሡ ፊት ተለወጠበት፥ አሳቡም አስቸገረው፥ የወገቡም ጅማቶች ተፈቱ፥ ጉልበቶቹም ተብረከረኩ።" ትንቢተ ዳንኤል 5፥5-6
"የተጻፈውም ጽሕፈት ማኔ፡ቴቄል፡ ፋሬስ ይላል። (ትንቢተ ዳንኤል 5፥25)

በመልአክ፥በራዕይ፥በአስገራሚ ጣት የእግዚአብሔር መልእክት (መልስ) ሲመጣ አየን። ለሙሴ ግን በእሳት ነበረ። "የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው፤እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። ... እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ ሙሴ ሙሴ፡ሆይ፡አለ..."
(ኦሪት ዘጸአት 3፥2-4)

በሕልም ሲናገር ደግሞ፦
"(ያዕቆብ) ሕልምም አለመ ፤ እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ፥ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ ፥ እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር። እነሆም እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት ነበር፥እንዲህም አለ..."
(ኦሪት ዘፍጥረት 28፥12)
"ዮሴፍም ሕልምን አለመ ለወንድሞቹም ነገራቸው፤...።"ዘፍጥረት 37፥5

የቅድስት ማሪያም እጮኛ ዮሴፍ በድንግሊቱ ጸንሳ መገኘት በተቸገረ ጊዜ ሕልም አየ። "እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርሷ የተጸነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።" (ማቴዎስ 1፥20-21)

የዚህ መልእክት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔር ድምፅ በብዙ አኳኋን ሊመጣ እንደሚችል ማሳሰብ ነው። ለዚህም የሚከተለው የመጽሐፍ ክፍል መሪህ ምሳሌ ይሆንናል፤ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ባይጻፍ ኖሮ ለማመን በተቸገርን ነበር። ይኸውም የበለዓም ታሪክ ነው። በለዓም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆነ ሁኔታ በአህያው ተቀምጦ ይጓዝ ነበር። "አህያይቱም የእግዚአብሔርን መልአክ አየች ከበለዓምም በታች ተኛች በለዓምም እጅግ ተቆጣ፥አህያዪቱንም በበትሩ ደበደባት። እግዚአብሔርም የአህያዪቱን አፍ ከፈተ ፥ በለዓምንም ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌብህ ነው? አለችው። ... እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ የእግዚአብሔርን መልዓክ በመንገድ ላይ ቆሞ፡ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ...።"
ዘኍልቁ 22፥27፥31

ዛሬም አህዮች የማይናገሩ ሆነው አይደለም። አህያችንም ወዳ አሰኘን አቅጠጫ አልነዳ ሲል ዱላ ከማንሣት የማንቆጠብ አንታጣም። ዐይኖቹ ከተከፈቱለት በቀር፡ ጉዞ በጠነከረ ቁጥር፡ ዱላ መምዘዝ የተለመደ ነው።

በለዓም እግዚአብሔር ዓይኖች እስከ ከፈተለት ድረስ ከአህያው ጋር እንደ ሰው ቆሞ ሲከራከር እንኳ አይደነቅም ነበር። *ባለቤቱን የሚደበድብ፥ልጆቹን የሚደበድብ፥ጓደኞቹን፥ ወንድሞቹን የሚደበድብ፥ቤተክርስቲያንና በመሥሪያ ቤት የሚደባደብ ፡ ገና ዓይኖቹ ያልተከፈቱለት የዘመኑ በለዓም ስንት ይሆን? እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን ይክፈትልን።*

ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች አምላካችን እግዚአብሔር ፀሎትን ሰምቶ ለመመለስ በብዙ አኳኋኖች ሊመጣ እንደሚችል አይተናል። ከተገለጸው ቃሉ ጀምሮ ወሰን በሌላቸው መንገዶች ሲናገረን ሰምተን በዕምነት ካልተቀበልን ቃሉ (እየመጣ) ሳይጠቅመን ይቀራል።

"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤... ዕብራውያን 1፥1-2

ጌታ ሲናገር የምንሰማው ስንቶቻችን እንሆን? በቅርቡ ድምፁን ሰምተን እናውቃለን? ድምፁን አለመስማት ይገደናል? ጌታን መስማት ለአንዳንድ ዕድለኞች እንጂ ለእኔ አይደለም ብለን ትተን ይሆን?

ጨዋና ዝግተኛው ድምፁ ኢየሱስን አምኖ ለተቀበለው ልባችን ሲሰማስ እንታዘዛለን? ለተጻፈው ቃሉ እንታዘዛለን?

እግዚአብሔርን ለመስማት ታላላቅ ድንቆችና ተዓምራት አያስፈልጉም። የተለመደ በሚመስሉት ዕለታዊ ክስተቶች ውስጥ ለሚጠባበቁት ይሰማል። ይታደግበታልም። አህያችን አልሄድ ሲል ዱላ ከመምዘዝ ይልቅ ሊያነጋግረን በዙሪያችን የቆመውን የጌታ መልዓክ ዞር ዞር ብሎ በፀሎት መፈለግ ይበጃል። መላኩም ተው፥ ተመለስ ቢል ፈጥኖ መመለስ አስተዋይነት ነው።

"ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፦ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት፥አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትም አርባ ዓመ ታትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ፥ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።" ዕብራውያን 1፥7-9)

ሰው እግዚአብሔርን መስማት እንዲችል በመጀመሪያ በጌታ በኢየሱስ ያለውን የንስሐ ሕይወት ተቀብሎ መጠበቅ አለበት፤ ከዚያም ሁልጊዜ ጆሮችን አቅንቶ መጠባበቅ ያሻል። የፀሎት መልስ፥ ልዩ ምሪት፥ ወይም ልዩ መረዳት ከእግዚአብሔር መስማት የሚወድ፦ ድምፁ በሚገኝባቸው ሥፍራዎች ፦ በቃሉ ንባብ ፥ በወንጌል ስብከት ፥ እግዚአብሔር በዕውነትና በመንፈስ ቅዱስ በሚመለክበት ሥፍራ ሁሉ ፥ ሆን ብሎ በመገኘት ማዳመጥ ያስፈልገዋል። የጌታ ድምጽ ለሚወዱትና ተግተው ለሚፈልጉት ሊገኝ ዝግጁ ነውና። እግዚአብሔር ይመስገን።



# ባሕሪይና ትዳር

ትዳርን ስናስብ ብዙ ጥንቃቄና ጥናት እናደርጋለን። ገና ሀሳቡ በልባችን ካደረበት ጊዜ ጀምረን እንፀልያለን። "የሚስማማኝን ባል/ ሚስት ስጠኝ" እያልን ያመን እንፀልያለን። ከዚያም ያ ሰው/ሴት የተገኘ ሲመስለን ፥ እግዚአብሔር ማረጋገጫ እንዲያሳየን እንፀልያለን። ዳሩ ግን እስከ ዛሬ ድረስ በምንም የማይጋጩ ባሕሪያት ያላቸው ባልና ሚስት አልታዩም። ምክንያቱም በሁሉ አንድ ዓይነት የሆኑ ሁለት ሰዎች ስላልተፈጠሩ ነው።

ሁለት የተለያየ ባሕሪይ ያላቸው ሰዎች በትዳር ሲጣመሩ፥የባሕሪያቸው ልዩነት በብዙ ወይም በጥቅቱ የሚደጋገፍ ወይም የሚጋጭ ይሆናል። የራሳችንንና የየትዳር ጓደኛን ባሕሪይ ተረድተን ፥ እንደ ጥሩ ቀማሚ በጥንቃቄ ብናስተባብረው ግን፦ እግዚአብሔርን አብረን የምናስከብር ሰላማዊ ቅንጅት የተሳካልን ባለትዳር እንሆናለን። ይኸ

ውም የመቀራረን ሕይወት ሳይሆን አንዱ የሌላኛውን ጉድለት ተረድቶ ለመሙላት የሚጥርበት የመቻቻልና የመረዳዳት ትዳር ይሆናል፡፡

ትዳር ሥራም÷ትምሕርት ቤትም÷ ማረፍያ ሥፍራም ነው፡፡ ይህም መሆን ያለበት ሞት እስከሚለያይ ነው ፡፡ ትጉሕ ገበሬ ሳያቋርጥ የእርሻውን ብልህት እየተማረ ÷ አረሙንም በጊዜው እየነቀለ÷ምርጡን ዘር በጊዜው እየዘራ በመከር ጊዜ አርፎ እንደሚበላ፡- ትዳርም እንዲሁ ነው ፡፡ የሚከተሉት ሀሳቦች የባሕሪይን ልዩነት በመረዳት ትዳርን የተሻለ ለማድረግ እንዲረዱ በጥናት የተዘጋጁ ናቸው፡፡

☼-- የራስህንና የባለቤትህን እውነተኛ ባሕሪይ እንዲገልጽልህ መንፈስ ቅዱስን ባለማቋረጥ ጠይቅ፡-

☼-- ባለቤትህ በአስተሳሰብና በተግባር ያንተ ካርቦን ቅጅ ብትሆን ደስተኛ የምትሆን መስሎህ ልትለውጣት አትሞክር፤ ይልቁን ልዩነቱ ትዳራችሁን የሚያበለጽግበትን መንገድ ለመረዳት ትጋ፡፡

☼-- ትዳርህን ብሩክና የተሳካ ለማድረግ አንተ ራስህ መማር ያለብህን ሁሉ እንዲያሳይህ መንፈስ ቅዱስን ዘወትር ጠይቀው፡፡ በእግዚአብሔር ፀጋ ዘወትር ለማደግና ባለቤትህንም በእድገቷ ለመርዳት ውሳኔና ጥረት አድርግ፡፡

☼-- በግልጽ ሳይነጋገሩ ይገባታል፡ይገባዋል፡ ብሎ ማሰብ ላለመግባባት መንሥዔ ስለሚሆን፡ የዘወትር መሻትህንና ስጋትህን ለባለቤትህ አጫውት፡፡ የእርስዋንም ሃሳብና ብሶት በጥሞና ስማ፡፡ ከዚያም አብራችሁ ጸልዩበት ፡፡ ሰው ሊያደርገው ወይም ሊሆን የማይችለውን ነገር ከባለቤትህ አትጠብቅ፡፡ ምንም ቢሆን የሰው ርካታና ሙላት እግዚአብሔር እንጂ ባል ወይም ሚስት አንዳይደለ መዘንጋት የለበትም፡፡

☼-- በሀሳብ ስትለያዩ አትደፋፈሩ፡፡ ይልቁን በትዕግሥት አስታራቂ ሃሳብ በመፈለግ አንዱ ሌላውን እንዲረዳ ይጣር፡፡ ነገር ከከረረ አንዱ ፈጥኖ ተረች ይሁን፡፡ ከሁለቱ የሚበረታው ለሰላም ሲል ፈቅዶ ይረታ፡፡

☼-- ለውሳኔ የሚያስቸግር ነገር ሲያጋጥም መልሱ እስኪመጣ በፀሎት መቆየት እንጂ በነገሩ ላይ መጣላት ለማንም አይጠቅምም፡፡

☼-- ፍቅር ለሰው ሁሉ የሚገባው በአንድ መንገድ ስላይደለ÷ባለቤትህ በሚገባት መንገድ ፍቅርህን ግለጽላት፡፡ ለምሳሌ አንተ ቁሳዊ ስጦታ ትወድ ይሆናል፡፡ ባለቤትህ ግን ከሥራ መልስ አረፍ ብለህ ብታጫውታት ከምንም አብልጣ ትወድ ይሆናል፡፡ እወቅበት!!

☼-- የቤታችሁ ኃላፊነት በአንዳችሁ ላይ ብቻ ጫና በማይሆንበት ሁኔታ ለመረዳዳት ተከፋፈሉት፡፡

☼-- ማንም ሳያቋርጣችሁ አብራችሁ ጊዜ የምታሳልፉበት ሁኔታ በቋሚነት ይኑራችሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ግጭት ሊያነሣሣ ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ጨዋታ (ንግግር) ራቁ፡፡ ከዚህ ይልቅ ሁን ብለህ ደስታ ያለበትን÷ሳቅ ያለበትን÷ ጭውውት ተጨዋወቱ፡፡

☼-- በመጨረሻም፡- ፍጹም የሆነ፡ችግር የማይከሰትበት ትዳር አለመኖሩን ዕወቅ፡፡ በሰላም የሚኖሩ ባለትዳሮች በጎረቤትህ ቢኖሩ፡- ስለሚቻቻሉ ብቻ ነው፡፡ ሰላምና ደስታን የሚፈልግ ሁሉ ከፍቅር በሚመነጭ መቻቻል ልቡንና ቤቱን መጠበቅ አለበት፡፡ በየትኛውም የሕይወት ዘርፍ መቻቻል የሚጠፋበትና ሁከት የሚነግሥበት ምክንያት ፍቅርን በጥንቃቄ ባለመጠበቅ ነውና፡፡ እኛ ወደ ሠላም የተጠራን ክርስቲያኖችም ሠላማችንን የምናጣበት ምክንያት ፍቅርን ባለመጠበቅ ነው ቢባል ስሕተት አይደለም፡፡

ለምሳሌ አብርሃምና ሣራ በዕውነት ይፋቀሩ ነበር፡፡ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- "እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም፡- ጌታ ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት፤ እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆቿ ናችሁ፡፡ እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ÷ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ ፤ ፀሎታችሁ እንዳይከለከል…" (1ጴጥ3÷6-7) እግዚአብሔር ትዳርህን የማረፍያ ሥፍራ ያድርግልህ፡፡ ለአንችም፡፡ የብዙዎችን÷ በተለይም የምዕመናንን ትዳር ለማወክ የተሰማሩ አጋንንት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የታሰሩ ይሁኑ፡፡ አሜን፡፡---------------------

# አባባ አብርሃም

አብርሃም አባታችን፡ ብሩክ የዕምነት ሰው
አምላክ ከሰው ልጆች፡ ለይቶ የጠራው

የአምላኩን ድምፅ ሰምቶ፡ ፈጥኖ የታዘዘው
ለምድር ነገዶች፡ በረከት የሆነው
እንዲህ ያለ ዕምነት፡ እንደምን ተቻለው?



እስቲ እንመርምረው፡ ይነግረን እንደሆን
የአበው ተመክሮ፡ ያካፍለን ሚሰጢሩን፡፡

አባባ አብራም
ባሕሪየ ርቱዕ፡ ልበ ቃና መልካም፡
ትጉህ የታራ ልጅ፡ ታማኝ የሦራ ባል፡
የዑር ምሥጉን ዜጋ፡ የሴም ትውልድ አባል፡፡

የይስሐቅ አባት
ጥሩ ዘመድ ወዳጅ፡ የእነ ሎጥ አጎት
ምሩጸ እግዚአብሔር፡ የያዕቆብ አያት፡፡

ያኔ ገና ያኔ፡ መጀመሪያው ዕለት
አሪት ዘፍጥረት፡ ምዕራፍ አሥራ ሁለት

በቁጥር አንድ ላይ፡ ጌታ ሲናገርህ
ከሐገር ከዘመድህ፡ ተለይልኝ ሲልህ
እኔን የማይገባኝ፡ የብዙዎችም ችግር
እንዴት ተቀበልኸው፡ ያላንዳች ክርክር?

ከምን አገኘኸው፡ እንዲህ ያለ ዕምነት?
አልተለማመድኸው፡እግዚአብሔርን መስማት
ያላለማመደህ፡ ወይ አባትህ ታራ
ድምፁን ሰምተህ ሳታውቅ፡ ከእናትህም ጋራ
በምን አርጎ ገባህ፡ የፈጣሪ ቃሉ?
ዛሬ ግን ብዙዎች፡ ግራ ይጋባሉ፡፡

ሞሬ ካድባሩ ዛፍ፡ በደረስህ ጊዜስ?
ሴኬም ላይ ዳግመኛ፡ ቃለ አምላክህ ሲፈስስ?
ከነዓንን ለዘርህ፡ ውርስ ሰጥቻለሁ
ለዘላለም በዚህ፡ ርስትህን አፀናለሁ
ባለህ ጊዜ ጌታ፡ ያልተጠራጠርኸው
እነዚያንስ አሕዛብ፡ ከቶ ያልፈራኸው
ልቤ ነው÷ቅዠት ነው÷ ሀሳቤ ያላልኸው
ንገረና አባባ፡ በምን ተረድተህ ነው?

እኛ በዚህ ዘመን፡ ጌታ ሲናገረን
በወንጌሉ ስብከት፡ ምክሩን ሲለግሰን
በሕልም÷በመገለጥ፡ መመሪያ ሲሰጠን
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ ተመለሱ ሲለን
ብዙ ምክንያት አለን፡ ቃሉን ላለማመን፡፡

ያውም እኮ ጌታ፡ ከእኛ ጋር ያደረረ
አማኑኤል በሙላት፡ ከእኛ ጋር የኖረ
አጽናኝ የተሰጠን፡ ሕዝቡም ያልታወረ

በዕድለኛው ዘመን፡ በዓመተ ምሕረት
ሰዉ እንዲህ ተስኖት፡ እግዚአብሔርን መስማት
ተነግሮትም ሰምቶም፡ እያልቻለ መውጣት
አንተ እንዴት በራልህ፡አብራም የእኛ አባት?
መስማት÷ማመንና እሽ ብሎ መውጣት?

አባታችን አብራም
በጥያቄዎቼ፡ ብዙ ሳትገረም
ስምህ ተለውጦ፡ አብርሃም ሲባል
እንደ ዛሬ ቢሆን ትንሽ ያስቸግራል
በበስተ እርጅና እንዲህ ይደረጋል?
ሕዝቡሳ ምን ይላል?
እባክህ ንገረን፡ ምን ተሰምቶህ ያውቃል?

እኛማ ሥልጡኖች፡ የዘመኑ ትውልድ
ፈጽሞ አንሞክርም፡ እንዲህ ያለውን ጉድ
እንኳንስ የስም ለውጥ፡ ባሕሪንም አንነካም
መታዘዝም ለውጥን፡ ከጠየቀ አንወድም፡፡
ሲሆን በመዋሸት፡ ደግሞም በማስመሰል
እንጂ መታዘዙን፡ ብዙ አይደል የሚችል፡፡

ስለዚህ ገርሞኝ ነው፡ አባታችን አብርሃም
ዕምነትን ከጻድቃን፡ ከአበው ምክርንም
አገኝ ብዬ ነው፡ እንዲህ መጠየቄ
የአማኝ ሁሉ አባት፡ መሆንክን አውቄ

የአይሑድ÷የክርስቲያን፡- የምዕመናን ሁሉ
አርዓያ ቅዱሳን፡ መታዘዝ ለቃሉ
በቅዱስ ድፍረትም፡ ባሥራትም ቀዳሚ
ጀግናና ተዋጊ፡ በተጠራህ ቋሚ፡፡

አምነህ÷ታዝዘህ÷ወጥተህ÷ኑረህ ያወረስኸን
ለመድኃኒ ዓለም፡ ትውልድ የሆንኸልን
የእስራኤል አምላክ፡ ተቀዳሚ ወዳጅ
አንተን መጠያየቅ፡ ለትውልድ የሚበጅ
የቅዱሳን ተምኔት፡ የእግዚአብሔር እፎይታ
አባባ አብርሃም፡ የትውልድ ደስታ፡፡

**ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡**